የአገልግሎቶችን ኢንዱስትሪዎች ሆነው ከአምስት በላይ ሠራተኞችን የያዙ ወይም የሚቀጥሩ እንዲሁም አጠቃላይ ካፒታላቸው ከብር 100 ሺህ እስከ 7.5 ሚሊየን የሆኑ ማለት ነው፡፡

## 2.2. የኦሮሚያ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ አክስዮን ማህበር የሊዝ ፋይናንስ አግግሎት የሚሰጣቸው ዘርፎች

### 2.2.1. የመፈብረኪያ ኢንዱስትሪዎች

**ሀ.** ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ማምረቻ
**ለ.** ቆዳና ሌጦ ስራ
**ሐ.** እንጨት፣ ጣውላና ብረታብረት ምርቶች ስራ
**መ.** ብረታብረትና ኢንጅነሪንግ
**ሠ.** የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረት
**ረ.** ፕላስቲክና የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት
**ሰ.** የሳሙና እና የንጽህና መስጫ ምርቶች
**ሸ.** ቀለሞች፣ ቫርኒሽና ማስቲሽ ምርቶች
**ቀ.** የጨርቃጨርቅና አልባሳት ማምረቻ እና የመሳሰሉት ናቸው

### 2.2.2. የኮንስትራክሽን /የግንባታ/ ኢንዱስትሪዎች

**ሀ.** ብሎኬት፣ቱቦና ጡብ ማምረቻ **ለ.** ኮንክሪት ፖል ማምረቻ
**ሐ.** ባዘላ ማምረቻ **መ.** ቴራዞ ማምረቻ
**ሠ.** ሴራሚክ ማምረቻ **ረ.** ጅብሰም ማምረቻ
**ሰ.** የግንባታ ዕቃዎች ማምረቻ እና የመሳሰሉት

### 2.2.3. የእርሻ ፕሮጅክቶች

**ሀ.** የመስኖ ልማት **ለ.** ንብ ማነብ መሳሪያ ማምረቻ
**ሐ.** የወተት ምርቶች **መ.** የዶሮ እርባታ ማሽነሪዎች
**ሠ.** የአሣ እርባታ እና የመሳሰሉት ናቸው

### 2.2.4. የእርሻ ውጤቶች ማቀነባበሪያዎች

**ሀ.** የወተት ተዋፅኦ ማቀነባበሪያ **ለ.** የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ
**ሐ.** የዶሮ ምርት ማቀነባበሪያ
**መ.** የቅመማ ቅመም፣ ከእፀዋት የሚገኙ መድኃኒቶችና ዘይቶች መጭመቂያና ማቀነባበሪያ
**ሠ.** የዓሣ ምርት ማቀነባበሪያ
**ረ.** የምግብ ዘይት መጭመቂያና ማቀነባበሪያ
**ሰ.** ምግብ ማቀነባበሪያ **ሸ.** የዱቄት ፋብርካ
**ቀ.** የዳቦ መስሪያና ማቀነባበሪያ እና የመሳሉት ናቸው

### 2.2.5.የሀገር ጉብኝት/የቱር ኢንዱስትሪዎች

ለጉብኝት አገልግሎት የሚውሉ መገልግያ መሳሪያዎች እንደ ጀልባና መኪና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 1.3. እሴቶች

⇒ ግልጸኝነት
⇒ የቡድን ስራ
⇒ ሃቀኝነት
⇒ ተጠያቂነት
⇒ አሳታፊነት

የኦሮሚያ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ አክስዮን ማህበር የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ለሚጠቀሙ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ዕቃዎች ፋይናንስ ኪራይ /የሊዝ ፋይናንስ/ እንዲሰጥ ከመንግስት ከፍተኛ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት ኩባንያው የሚከተሉትን ዓላማዎች የሚያሳኩ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ኪራይ ፋይናንስ ያደርጋል፡፡

◊ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት ለሚሰሩ፣
◊ የሥራ ዕድል በብዘት/በስፋት/ ለሚፈጥሩ
◊ ወደ ውጭ ሀገራት ምርቶችን በማምረትና የመላክ ሀገራዊ ዓለማን የሚደግፉና የውጭ ምንዛሬን የሚያስገኙ፣
◊ ዋስትና ለማቅረብ ባለመቻልና በተለያዩ ምክንያቶች የፋይናንስ ድጋፍ ላላገኙ አነስተኛና መካከለኛ (Missing Middle) ኢንተርፕራይዞች፣ እና
◊ የመዋቅር ሽግግር (Transformation) የሚደግፉ

## 2. የሊዝ ፋይናንስ እና ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ትርጉምና አገልግሎቶች

## 2.1. ትርጉም

**ሀ. ሊዝ ፋይናንስግ**

ሊዝ ፋይናንስግ ማለት ኩባንያው ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃዎችን ገዝቶ በዱቤ ግዥ ሥርዓት (Hire purchase lease) ሞዳሊቲ ለኪራይ የሚያቀርበው አገልግሎት ነው፡፡

**ለ. ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች**

የኦሮሚያ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ አክስዮን ማህበር ከተሰጠው ተልዕኮ አንፃር ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ የመፈብረክ፣ የኮንስትራክሽን፣ የግብርና ሥራችን፣ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ወይም አግሮ ፕሮሴስንግ፣ የሀገር ጉብኝት፣ የማዕድን እና ቁፋሮ (Mining and Quarries) እና

**W.A.DALDALA FAAYINAANSII MEESHAALEE KAAPPITAALAA OROMIYAA**

**ኦሮሚያ የካፒታል ዕቃዎች ንግድ አ.ማ**

**OROMIA CAPITAL GOODS FINANCE BUSINESS S.C.**


**አድራሻ**

**አዳ ታዎር፣ ካዛንቺስ፣ አዲስ አበባ**

**2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር - 208**
**3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር - 301**

**ስልክ: + 251 11 557 1337/07**

**ፋክስ: +251 115 57 1411**


## 1. መግቢያ

የኦሮሚያ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ አክስዮን ማህበር የመንግስት የልማት ድርጅት (ፋይናንስ ተቀም) ነው፡፡ ኩባንያው የሚከተሉት ተልዕኮ ራዕይና እስቶች አሉት፡-

## 1.1. ራዕይ

በ2022 ዓ.ም በኢትዮጵያ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ከምሰጡት ተቋማት መካከል ሞዴልና ተመራጭ ተቋም ሆኖ ማየት

## 1.2. ተልዕኮ

በተለያዩ ስራ ዘርፎች ላይ ለመሰማራት ፍላጎት፣ ሙያና ዕዉቀት ኖሯቸዉ ነገር ግን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ዕጥረት ላለባቸው ኢንተርፕራይዞች በተመጣጣኝ ዋጋ የካፒታል ዕቃዎችን በመግዛት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡

#### 2.2.6. የማዕድነት ልማት (Mining and Quarries)

**ሀ.** ዕብነበረድ ማምረቻ
**ለ.** ወርቅና የከበሩ መዕድናት ማምረቻ
**ሐ.** ጠጠር ማምረቻና እና የመሳሰሉት ናቸው

### 2.3. የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎቶች

ኩባንያው የሊዝ ፋይናንስ አግልሎት የሚሰጣቸው ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራዞች ሆነው በመንግስት የኢኮኖሚ የትኩረት መስኮች ላይ የሚሰሩና የካፒታል ዕቃዎችን ለፕሮጄክቶቻቸው መጠቀም የሚችሉ መሆን አለባቸው።

- ኩባንያው ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለማምረት የሚያገለግሉ የካፒታል ዕቃዎችን ገዝቶ በኪራይ መልክ ያቀርባል።
- የሚሰጠው የካፒታል ዕቃዎች የሊዝ ዋጋ መጠን አስፈላጊ በሆኑባቸው ዕቃዎች ተከላና ሥልጠና ለሚያስፈልጉ ዕቃዎች የትራንስፖርትና የስልጠና ድረስ ያሉ ወጪዎችን ያጠቃልላል።
- ከወጪ ለሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ዕቃው ከታዘዘበት ዕለት አንስቶ እቃው ለተረከቡበት ጊዜ መሀከል ያለው ኩባንያው ለአስመጪው ለከፈለው ዋጋ ላይ የአገልግሎት ክፍያ ተደምሮ ከመደበኛው የወለድ መጠን ክፍያ በየወሩ ወይም በየሦስት ወሩ እንደ ክፍያ መርሀግብር ጋር ይከፍላል።

### 2.4. ለካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ተጠቃሚነት ብቁ የሚያደርጉት መስፈርቶች

ኩባንያው የካፒታል ዕቃዎች በኪራይ ለማግኘት የሚፈልጉ አዲስ ደንበኞች መሟላት የሚጠበቅባቸው መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው።

- አመልካቹ ለኪራይ ብቁ መሆንና የሚያቀርበው ፕሮጀክትም ኩባንያው መሰፈርት የሚያሟሉ እንዲሁም አዋጭነት የተጠና መሆን አለበት።
- አመልካቹ የቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው መስኮች ከላይ በተ.ቁ 2.2 ላይ የተጠቀሱት ላይ የሚሰራና የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር፣የታደሰ ንግድ ፍቃድ፣ንግድ ፍቃዱ በይነመረብ ላይ የተመዘገበ (Online Registration) ያለው መሆን አለበት
- አመልካቹ በፕሮጅክቱ ላይ ያለው ዕውቀትና ግንዛቤ ለመለካት የሚረዳ እስከ 5 ሚሊየን ብር የሚያወጣ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ለሚጠይቅ ፕሮጀክት በጥራት የተዘጋጀ የቢዝንስ ዕቅድ (Business Plan) ማቅረብ አለበት
- አመልካቹ ለፕሮጅክቱ የሚበቃ መሰረተ ልማት ያሟላና መስሪያ ቦታ ማቅረብ አለበት። የመስሪያ ቦታ ኪራይ ከሆነ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ህግዊ ውል ማቅረብ ይኖርበታል
- አመልካቹ ኩባንያው የሚጠይቀውን አሰፈላጊ ሰነዶች ተገቢ የሆኑ ማስረጃዎችን እና ወቅታዊ የታክስ ክፍያ ኪሊራንስ ማቅረብ ይኖርበታል።

### 2.5. የካፒታል ዕቃ በኪራይ ለመውሰድ የአመልካቾች መዋጮ

ኩባንያው የካፒታል ዕቃዎችን እንጂ ተያያዥ ወጪዎችን ፋይናንስ አያደርግም፤ በሌላ በኩል አመልካቹ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ የሥራ ማስኬጃ ማለትም የደመዎዝ፣ የጥሬ ዕቃዎች የጥሬ ዕቃዎች ግዥ፣ የቢሮ ኪራይ፣ የቢሮ መገልገያዎችንና የመሰሰሉ ወጪዎች አይሸፍንም፣

- ኩባንያው ከፍተኛው የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ /የሊዝ/ ዋጋ 80 በመቶ እና በተከራይ የሚያዋጣው አስፈላጊው የ20 በመቶ ይሆናል፣
- አመልካቹ የሚፈለግበትን የ20 በመቶ የገንዘብ መዋጮ የካፒታል ዕቃው ዋጋ ከተለየ በኃላ የካፒታል ዕቃ ውል ከመፈራረሙ በፊት ኩባንያው በከፈተው ዝግ የሂሳብ አካውንት ገቢ ማድረግ አለበት። የተከራዩ መዋጮ ገቢ ሳይደረግ የዕቃዉ ግዥ አይፈፀምም።

### 2.6. የአግልግሎት መጠን ክፍያዎች

- ተከራዩ የሊዝ አገልግሎት ክፍያን በተቀመጠለት የጊዜ መክፈያ ማለትም በወሩ ወይም በየሶስት ወሩ መክፈል ይኖርበታል፣
- ወቅታዊው የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት ክፍያ መጠን 15% በመቶ በዓመት በዲክላይን የሂሳብ ስሌት ነው።

### 2.7. የካፒታል ዕቃዎች ግዥ ሥርዓት/ፕሮሲጀር

- የካፒታል ዕቃዎች ግዥ የሚፈፀመው አመልካቹ በሚያቀርበው የካፒታል ዕቃው ዝርዝር ስፔስፊኬሽን፣ የዋጋ ማቅረቢያ እና ምርጫ መሰረት ነው።
- ኩባንያው ምንም እንኳ በአመልካቹ ምርጫ ላይ የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ቢሆንም በሚገዛው የካፒታል ዕቃ ላይ ለሚፈጠረው የጥራት ጉድለትና እንከን ኃላፊነት አይወስድም፣ የጥራት ጉድለት እንከን ለዕቃው ኪራይ አለመክፈልም ምክንያት አይሆንም።
- ኩባንያው ግዥ የተፈፀመለትን የካፒታል ዕቃ አምራቹ ወይም ከአቅራቢው ወደ ተከራዩ መድረሱንና መተከሉን ይከታተላል፤ በመጨረሻም መስራቱን አረጋግጦ ለከተራዩ ያስረክባል።

### 2.8. የፋይናንስ ዕቃዎች የመድህን ዋስትናና ጥገና

- ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን መጠበቅና መንከባከብ ይኖርበታል፣
- ተከራዩ ከኩባንያው ከሚሰጠው የፅሑፍ ስምምነትና ዕውቅና ውጪ የካፒታል ዕቃውን ለሌላ ሥራ መጠቀም አይችልም፣
- ተከራዩ የተከራየውን የካፒታል ዕቃ በተቀመጠለት የጊዜ ሴለዳ መሰረት ተቀባይነት ባለው የሰርቪስ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ማስደረግ ይኖርበታል
- ተከራዩ ለተከራየው የካፒታል ዕቃ በኩባንያው ስም የመድን ዋስትና ይገባለታል፤ የሊዝ ጊዜው እስከሚበቃ ድረስ የመድን ዋስትና ውሉን በየጊዜው የአረቦን ክፍያውን እየከፈለ ማደስ አለበት።

### 2.9. የሊዝ ኪራይ እና የወለድ ክፍያ ጊዜ

- የሊዝ ክፍያ ጊዜ የሚወሰነው በእያንዳንዱ ፕሮጀክት የገንዘብ ፍሰት (Cash flow) እና በካፒታል ዕቃው የአገልግሎት ዘመን መሰረት ሆኖ የሊዙ የቆይታ ጊዜ ከስድስት ዓመት መብለጥ የለበት።
- ለክፍያ የደረሰው የሰርቪስ አገልግሎት ዋጋ ከዋናው ኪራይ ክፍያ ጋር በተቀመጠለት የክፍያ ሰሌዳ መሰረት መክፈል ይኖርበታል።

### 2.10. የከራይ መጠን

- ለአንድ የካፒታል ዕቃ ተከራይ በአንድ ጊዜ ወይም በተለያየ ጊዜያት የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጠው የገንዘብ መጠን ከ5 ሚሊየን ብር መብለጥ የለበትም። የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሊዝ ፋይናንስግ አገልግሎት በሙሉ የሚሰጠው በዓይነት ብቻ ይሆናል።
- ለአንድ ካፒታል ዕቃ ተከራይ ሊሰጥ የሚችለው ዝቅተኛው የሊዝ ፋይናንስንግ አገልግሎት መጠን ሃምሳ ሺህ (50,000.00) ብር ነው።

### 2.11. የኩባንያው ቅ/ጽ/ቤቶች አድራሻ

| | |
|---|---|
| * ቡራዩ - 0112604444 | * አምቦ - 0112609310 |
| * ሰበታ - 0113662727 | * ወሊሶ - 0113664317 |
| * ለገጣፎ - 0118932434 | * ጂማ - 0478119161 |
| * ቢሾፈቱ - 0118487031 | * መቱ - 0471411993 |
| * አዳማ - 0228119169 | * ነቀምቴ- 0578619280 |
| * ሻሸመኔ - 0462115171 | * ጊምቢ - 0577712310 |
| * አሰላ - 0228319044 | * ፊቼ - 0111609178 |
| * ሐረማያ - 0258611493 | |